# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 248 የካቲት 7 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

> ህግ የሚወጣው መንግስት የዜጎችን መብት ለመጠበቅ ነው፤ በወያኔ ግን "ህግ" ማለት የመንግስት መሳሪያ ዜጎችን መጨፍለቂያ ስልጣንን ማሰንበቻ ነው። በሀገራችን የመናገር መብት ተገፎ እያለ የማምለክ መብት ሊፋፋ አይችልም፤ ወይም ደግሞ ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብት ተጥሶ እያለ የማምለክ መብትን የሚያስከብር ተቋም ሊኖር አይችልም።
>
> ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## መሪ አልባዉ የወያኔ ሚኒስትሮች ምክር ቤት በስንዴ ግዢ ጉዳይ ሲጨቃጨቅ መከረሙ ተሰማ

ከዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ሞት በኋላ ይህ ነዉ ተብሎ የሚጠቀስ መሪ የሌለበት የወያኔ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ተብየው መፈራራትና መከባበር የሚባል ነገር ርቆት አባላቱ "ፕሮፓጋንዳ ይሻለናል" ወይስ "ሀቁን ተጋፍጠን መፍትሔ እንፈልግ" በሚሉ ሁለት ቡድኖች ተከፍሎ በየቀኑ ሲጨቃጨቅ እንደሚዉል ለካቢኔዉ ቅርበት ያለቸዉ የታመኑ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩልን ዜና ገለጹ። የስንዴው ፖለቲካ በሚል አርዕስት ለዝግጅት ክፍላችን በደረሰዉ ዜና መሰረት የወያኔ አገዛዝ አገሪቱ ዉስጥ በኤኮኖሚዉና በማህበራዊ ዘርፎች እየደረሰ ያለዉን ቀዉስ መቆጣጠር አቅቶት አሁን ስራዬ ተብሎ የተያያዘዉ የእህል ውድነት በህዝቡ ላይ በተለይ ወያኔ ለስልጣኔ ያሰጋኛል ብሎ በሚፈራዉ በከተማዉ ህዝብ ላይ ያስከተለውን ቀውስ በአስቸኳይ "ለማረጋጋት" ምን ያህል ስንዴ ከውጭ እንግዛ በሚል ጭቅጭቅ መሆኑን ዉስጥ አዋቂ ምንጮቹ አክለዉ በላኩልን ዜና ገልጸዋል ።

በዚህ ሳምንት ከወያኔ ጓዳ በደረሰን ዜና መሰረት የዋጋ ግሽበቱን ለመቆጣጠር በሚል በያዝነዉ ወር 850 ሺህ ኩንታል ስንዴ አገር ውስጥ ገብቷል። የዚህ ከፍተኛ የዉጭ ምንዛሬ ወጥቶበት የተገዛዉ ስንዴ ጉዳይ ቀድሞዉንም በቋፍ የነበረዉን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጭራሽ ዱላ ቀረሽ ጭቅጭቅ ዉስጥ እንዲዘፈቅ አደርጎታል። በአንድ በኩል ግዢዉ የሚፈጥረዉ የዉጭ ምንዛሬ ጉድለት የባሰዉኑ የዋጋ ግሽበቱን ያባብሰዋል የሚሉ የካቢኔዉ አባላት ሲኖሩ በሌላ በኩል ደግሞ "ባለፉት ሶስት ዓመታት ብቻ ከ1.6 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን በላይ ስንዴ ከውጭ አምጥተን አከፋፍለናል ሆኖም ምንም አይነት ዘለቄታዊ ለውጥ ማምጣት አልቻልንም ብለዉ የሚከራከሩ እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል።

ቁጥራቸዉ ትንሽ ቢሆንም ከእነዚህ ሁለት ቡድኖች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአማራው የጸረ ሙስና ኮሚሽን በሙስና መከሰሱ ተሰማ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው ከመሬት ሽያጭ ጋር በተያያዘ በክልሉ የሚታየው ከፍተኛ ሙስና ሊገታ ያልቻለው የክልሉ ጸረ ሙስና ኮሚሽን በሙስናው ዋና ተዋናይ ሆኖ በመገኘቱ ነው በማለት በአማራ ክልል የሚሰሩ የተለያዩ የመንግስት መስሪያቤት ሰራተኞች እና የወያኔ ኢህአዴግ አባላት ለኢሳት እንደገለጡ ዘግቡአል።

ሰራተኞቹ ከወራት በፊት ከፍተኛ የዜና ሽፋን ተሰጥቶት የነበረውን የሙስና ጉዳይ በማንሳት እንደገለጡት፣ የክልሉ ባለስልጣናት ከባለሀብቶች ጋር በመመሳጠር በባህርዳር ከተማ ከፍተኛ የሆነ የመሬት ችብቸባ እያካሄዱ ቢሆንም፣ የክልሉ የጸረ ሙስና ኮሚሽን በሙስና ተወናይ በመሆኑ አደጋውን ለመከላከል አልተቻለም ብሉአል ኢሳት በዘገባው።

እንደ ኢሳት ዘገባ በመሬት ላይ የሚካሄደውን ዘረፋ የሚመሩት የከተማው የኢንዱስትሪ ልማትና ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ሰራተኞች የሆኑት አቶ ገብሩ ጸሀይነህ፣ አበበ ሰማ፣ አየነው አለሙና በጊዜው ጸሀየ መሆናቸውን ሰራተኞች ይገልጣሉ።

የክልሉ የጸረ ሙስና ኮሚሽን መርማሪ የሆነው መቶ አለቃ እንዳለው አራቱ ግለሰቦች የከተማውን መሬት በድርድር በመሸጥ የሚጠረጠሩ መሆናቸውን በመግለጽ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ መደረጋቸውና አርብ ጥቅምት 30/2005 ዓም ለይስሙላው ፍርድ ቤት ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ መደረጉን መግለጹ ታውቋአል።

አራቱ ተከሳሾች ፍርድ ቤት ሲቀርቡ በከተማዋ የሚገኙ ባለሀብቶች ፍርድ ቤቱን ያጨናነቁ ሲሆን፣ ዳኛውም የተከሳሾችን ፋይል አይቶ ውሳኔ ያሰጣል አያሰጥም በማለት ለመወሰን የጊዜ ቀጠሮ ሰጥቶ ፋይሉን ወደ መዝገብ ቤት ከመራ በሁዋላ፣ የጸረ ሙስና ኮሚሽነሩ ተከሳሾች የዋስትና መብት ይፈቀድላቸው የሚል ደብዳቤ ዳኞች እንደገና ችሎት እንዲሰየሙ ተደርጎ ተከሳሾቹ እያንዳንዳቸው በ5 ሺ ብር ዋስ እንዲለቀቁ ተደርጓል ብሉአል ኢሳት በዘገባው።

## ከፍተኛ የህዝብ ተቃውሞ ጭንቀት የፈጠረበት ዝዘረኛ የወያኔ አገዛዝ በትናንትናው እለት ሞባይል ኔትወርክ አቋርጦ እንደነበር ታወቀ

ላለፈው አንድ አመት በጽናት የተቃውሞ ድምጻቸውን በማሰማት ላይ የሚገኙት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን የፈጠሩበት ጭንቀት ያደናበረው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ ከጁምአ ጸሎት ስርዓት ጋር ረብሻና ከፍተኛ ተቃውሞ ሊነሳ ይችላል በሚል ስጋት ትናንት ማለዳ በአዲስ አበባ የሞይባል አገልግሎት ከአምስት ሰዓታት በላይ እንዲቋአረጥ አድርጎ እንደነበር ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ገለጸ፡፡

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ከጊዜ ወደጊዜ በጽናት ድምጻቸውን የሚያሰሙት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን በመደበኛ የጁምአ ፕሮግራማቸው እርስ በእርስ በመጠራራት እና አጫጭር የስልክ መልዕክቶችን በመለዋወጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ሊያደርጉብኝ ይችላሉ በሚል ፍርሃት ሐሙስ ለዓርብ አጥቢያ በግምት ከለሊቱ 10 ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ 4:00 ሰዓት ድረስ የተወሰኑ የሞባይል ሰልክ ቁጥሮችን ከግንኙነት ውጪ የማድረግና ኔትወርክ የማቋረጥ እርምጃንም ወስዱአል፡፡

የህዝብ መንገላታት ደንታ የማይሰጠው የወያኔ አገዛዝ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ ያነጣጠረ ርምጃው በበርካታ ግለሰቦችና የቢዝነስ ተቋማት ላይም ተመሳሳይ ተጽእኖ በማሳደሩ የእርስ በርስ ግንኙነት ማድረግ ሳይችሉ ለማርፈድ መገደዳቸውን ዘጋቢያችን አያይዞ ገልጹአል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ሁሉም የሞይባል አገልግሎት ያልተቋረጠበት ዋንኛ ምክንያት ምን እንደሆነ ለጉዳዩ ቅርበት ካላቸው ምንጮች ባገኘው መረጃ የተወሰኑ የደንበኛ ጭነት ያለባቸው መስመሮች ግንኙነት ከተቋረጠ ያልተቋረጠባቸው ስልኮች ከእነዚህ ጋር ግንኙነት ማድረግ አይችሉም ማለታቸውን ገልጹአል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ቁጥሮች አለመቋረጣቸው ቴሌ ለሚነሳበት ቅሬታ የኔትወርክ መጨናነቅ ነው በሚል ጉዳዩን ለማስተባበል ስለሚረዳው ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑን እነኝሁ ምንጮች መጥቀሳቸውንና የዚህ ዓይነቱ አሰራር ሲፈጸም የመጀመሪያው አለመሆኑን ማመልከታቸውን ኢሳት ገልጹአል፡፡

## የሚልየኒየሙ ግድብ በያዝነዉ ሚለንየም ዉስጥ ተገንብቶ ማለቁ አጠራጣሪ ነዉ ተባለ

ከቀድሞዉ ዘረኛና አምባገነን የወያኔ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ሞት በኋላ የሚድያ ሽፋኑን፤ የገንዘብ ምንጬንና አጋራዊ ትኩረቱን በከፍተኛ ፍጥነት እያጣ የመጣዉ የህዳሴዉ ግድብ እንኳን በስድስት አመት በስድት ግዜ ስድስት አመትም ተገንብቶ ማለቁ እጅግ በጣም አጣራጣሪ ነዉ እያሉ አያሌ የገዢዉ ፓርቲ አባላት በግልጽ በመናገር ላይ መሆናቸዉን የአዲስ አበባ ዘጋቢዎቻችን ለኢህአዴግ ቅርበት ያላቸዉን ምንጮች በመጥቀስ በላኩልን ዜና ገለጹ። መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረባቸዉ የመጨረሻዎቹ ሁለት አመታት በኢትዮጵያ ቴሌቭዢንና ሬድዮ በየቀኑ ይጠቀስ የነበረዉ የህዳሴዉ ግድብ ዛሬ ጭራሽ ስሙን የሚያነሳዉ በመጥፋቱ አንድዳንድ ሰዎች ግድቡ ተሰርቶ አለቀ እንዴ ብለዉ እንዲጠይቁ አድርጓቸዋል። የህዳሴዉ ግድብ ግንባታም ሆነ የሚድያ ሽፋን ለምን እንደቀዘቀዘ የገዢዉ ፓርቲ ካድሬዎችም ሆኑ የመለስን ራዕይ ከግብ አድርሳለሁ ብሎ ቆርጦ የተነሳዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ለመናገር ፈቃደኛ ባይሆኑም እንደ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ግምት ቀድሞዉንም ቢሆን ግድቡ የተጀመረዉ በወቅቱ ወያኔን አጣድፎ የያዘዉን የፖለቲካ ራስ ምታት ለማቀዝቀዝ ነዉ እንጂ የአገሪቱ የገንዘብ፤ የቴክኒክና የድርጅት ብቃት ታይቶ አልነበረም።

ከሰማንያ ቢሊዮን ብር በላይ የተገመተዉ የህዳሴዉ ግድብ ተገንብቶ ይጠናቀቃል ተብሎ የታመነዉ ሙሉ በሙሉ ከአገር ዉስጥ ምንጮችና ዉጭ አገር ከሚኖሩ አትዮጵያዉያን በሚገኝ ካፒታል ሲሆን ባለፉት ሁለት አመታት ለህዳሴዉ ግድብ ግንባታ በተለያየ መልኩ አገር ቤትና ዉጭ አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን የተሰበሰበዉ ገንዘብ ስምንት ቢሊዮን ብር ወይም ለግንባታዉ ከሚያስፈልገዉ ገንዘብ 10 በመቶ ብቻ ነዉ። አንድ በግድቡ የዲዛይን ስራ ላይ የተሳተፉ መሐንዲስ ለዘጋብያችን እንደተናገሩት የህዳሴዉ ግድብ ችግር ትኩረቱ እየቀነሰ መምጣቱና ገንዘብ አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የግድቡ ግንባታ በአገሪቱ ኤኮኖሚ ላይ የፈጠረዉ ከፍተኛ ጫና ሌሎች አንገብጋቢ ፕሮጅቶች እንዳይጀመሩ ወይም የተጀመሩት ቆመዉ እንዲቀሩ ማድረጉ ነዉ ብለዋል። ይህን በተመለከተ የአለም ባንክና አለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ኢትዮጵያ የጀመረቻቸዉን የተለያዩ ፕሮጀክቶች ማስጨረስና አገሪቱን ቀስፎ የያዘዉን የዋጋ ንረት ለመቀነስ ከፈለገች የህዳሴዉን ግድብ ግንባታ ለተወሰነ ግዜ ማቆም አለባት ብሎ መምከሩ የሚዘነጋ አይደለም። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ግፍ ሲበዛ ማስፈራት፤ እስርም ሲበዛ ማሸማቀቁ ይቀራል

የወያኔ ልብ ወለድ “ደራሲዎች” ተደራሲ በሌለበት አለም ሆነው የገሃዱን አለም ነጸብራቅ ያልሆነውን የቀን ቅዠታቸውን በመርዛማና በዶለደመ መቃቸው ዛሬም እንደትላንቱ በቆሸሸው ኢቲቪ አማካይነት የጥጋብ ግሳታቸውን ማግሳት ቀጥለዋል፡፡ እኛም ግሳታቸውን በተራብ አንጀት እነሆ ለ21 አመት እየተጋትነው አለን።

የወያኔ ዘረኞች ቀደም ሲል በግንቦት 7 እና በሌሎቸም ደርጅቶች ላያ ያነጣጠሩ አኬልዳማን የመሰሰሉ የዉሸት ድራማዎችን በማቀነባበርና ሀአዲስ አበባን እንደ ባግዳድ የእልቂት ቀጠና ሊያደርጓት ነዉ የሚል የሞት ዜና ለህዝብ በማሰማት የታጋዮችን ቅስም ለመስበርና የህዝብን የተነሳሳ የትግል ስሜት ለማቀዝቀዝ ከፍተኛ ሙከራ አድርገዋል።

እነዚህ ዘረኞች በባህላችንም ሆነ በሀይማኖታችን እንዲሁም በኢትየጵያዊ ትውፊቶቻችን ላይ ሲያላግጡ ገና ከመጀመርያው በቃቸሁ በለመባላቸው ዛሬም እንደትናንቱ “የምን ትሆናላችሁ” ንቀታቸዉንና ለህዝብና ለአገር ያላቸዉን ጥላቻ ትውፊቶች ያላቸውን ጥላቻና ንቀጅሃዳዊ ሃረካት፡ በሚል የዘግናኝ ፊልም እያሳዩንነው። ጅሃዳዊ ሃረካትን ከአኬልዳማ የሚለየዉ ነገር ቢኖር፤ ጅሃዳዊ ሃረካት፡ ለዘመናት ተከባብረው በኖሩት የሀገራችንን የእምነት ተቋማት ላይ ያነጣጠረ መሆኑ ነው፤ ይህ የወያኔ ጭፍን ተግባር የሚያሳየን ወያኔ ስልጣኑን እስካራዘመለት ድረስ ምንም ነገር ከማድረግ የማይመለስ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ተከባብሮ የኖረን ህዝብን፣ እምነትንና አገራችንንም ጭምር ለማጥፋት እንደማይመለስ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ እውነታውን ወይም ሀቁን ለይቶ የሚረዳና የሚያገናዝብ ህዝብ በመሆኑ እንጅ የወያኔ ቆሻሻ መልቀቂያ በሆነው በኢቲቪ የሚተላለፉትን ድራማዎች ወይም ውሸቶች፣ ከንቱ ትረካዎችና አንድን ህዝብ በሌላው ላይ እንዲሁም አንዱ ሃይማኖት በሌላው ሃይማኖት ላይ እንዲነሳ ለማድረግ ያደረጋቸዉ ሙከራዎች አገራችን ኢትዮጵያን የት ሊያደርሳት ይችል ነበር ብለን ስንገምት በኢትዮጵያ ህዝብ ጽናትና አርቆ አስተዋይነት ህዝብ እንድንኮራና እንድንተማመን ያደርገናል፡፡

በተቃራኒው ወያኔ እራሱ አገር ምድሩን እያሸበረ ሌሎች ለመብታቸው የሚታገሉ ወገኖቻችንንችን በተለይም የአስልምና እምነት ተከታይ ወንድሞቻችንን ሽብርተኞች ናችሁ እያለ በማሰሩ አፍረንበታል።

ወያኔ ይህንን የሚደርገው የታጋዮችን ቅስም ለመስበር ብቻ ሳይሆን ሌሎች ወጣቶች የታጋዮችን አርአያ ተከትለው ትግሉን እንዳይቀላቀሉና የስልጣን እድሜውን እንደያሳጥሩበት ለመቀጣጫ እንዲሆንና ወጣቱን ከትግሉ መንደር ለማራቅ ቢሆንም እውነታው ግን የሚያሳየው የተገላቢጦሽ ነው፡፡ ግፍ ሲበዛ ማስፈራቱ፣ እስርም ሲበዛም ማሸማቀቁ ይቀራል፡፡ በዛሬዩቱ ኢትዮጵያ እስርም ሆነ ግርፋት የማይፈራበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። ዛሬ የኢትዮጵያ ወጣቶች እኔ አቡበከር ነኝ እኔ አንዷለም ነኝ እያሉ ተነስተዋል፤ ይህም የወያኔ መውደቀያ ቀን አብይ ምልክት ነው።

ህወሃት አሸባሪ ድርጅት ነው። ህወሃት የማህበረሰባችን የእምነት ነጻነት፤ ክብርና መብት የሚገፍ፣ የሚያዋርድ፣ የሚያፈናቅል ጤነኛ ያልሆነ ስርአት በመሆኑ መብታችንና ነጻነታችንን ለማስከበር ማናቸውንም አይነት የትግል ስልት ተጠቅመን ወያኔን በመፋለም ህዝባችንን ከእርስበርስ ግጭት፤ አመጽና ትርምስ የማዳን ግዜው አሁን ወይም ዛሬ ነው ይላል ግንቦት 7።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነት የዲሞክራሲ ንቅናቄ ትላንት እንዳልነው ዛሬም ለመብታቸው ሲሉ በወያኔ እጅ ለሚሰቃዩ ወገኖቻችን ያለንን ጥልቅ አክብሮት ይገልጻል፡የኢትዮጵያ ህዝብ ለነጻነቱ፣ ለማንነቱ፣ ለእምነቱ፣ የሚያደርገው መራራ ትግል ይቀጥላል። የህወሃት መርዘኛ አፈ ሙዞች ወይም የጅል ፕሮፖጋንዳ ድራማዎች ትግሉን ለደቂቃም ቢሆን አይገቱትም ያጠናክሩታል እንጂ፡፡ ወያኔ የህዝብን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ ጠያቂዎቹን በሀሰት የሚወነጅል ጀሃዳዊ ሀረካት ብሎ ያረበዉን ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አጥብቆ ያወግዛል፡፡

የድራማው ሌላኛው መልእክት በኢትዮጵያ ውስጥ የፍትህ ስርአት ሞቶ የተቀበረና የማይነሳ መሆኑን ቀባሪው ወያኔ የቀብሩን ስነስርአት በቲቪ መስኮት እነ አኬልዳማን፣ ጀሃዳዊ ሀረካትን ካለ ከልካይ እርሱ የሚጮኸው ጩኸት ትክክል መሆኑን ያሳየናል፣ ደጋግሞም ይነግረናል። ልብ ይበሉ የአሻንጉሊቱ የፍርድ ቤት ዳኞች የተባሉት በዚህ የቀብር ስነስርአት በየትኛው የአስለቃሽ ቦታ ላይ መሆናቸውን ግን ድራማው አያሳየንም።

ህግ የሚወጣው መንግስት የዜጎችን መብት ለመጠበቅ ነው፤ በወያኔ ግን “ህግ” ማለት የመንግስት መሳሪያ ዜጎችን መጨፍለቂያ ስልጣንን ማሰንበቻ ነው። በሀገራችን የመናገር መብት ተገፎ እያለ የማምለክ መብት ሊፋፋ አይችልም፤ ወይም ደግሞ ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብት ተጥሶ እያለ የማምለክ መብትን የሚያስከብር ተቋም ሊኖር አይችልም።

ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የዛሬ ሁለት አመት ወያኔዎች አኬልዳማ የተሰነውን አማተርና ደካማ ድራማቸውን እንደፈለጉ በሚቆጣጠሩትና በሚያዙት የውሸት መፈብረኪያ ቴሌቪዥናቸው ሲያሰራጩ እንዲህ አይነቱን ንቀትና ውርደት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስቆምና የዘረኛ አምባገነኖችን ትእቢት ለማስተንፈስ ትግሉን አጠናክሮ በመቀጠል ወያኔን ለማስገደድና ለማስወገድ ቀን ከሌሊት በመስራት ላይ ይገኛል። ስለዚህም ሙስሊሙ ወገናችንም ሆነ ህዝበክርስትያኑ ሰብአዊ መብቶች ሳይከበሩ የሃይማኖት ነጻነት ብቻውን ሊከበር የማይችል መሆኑን ተረድቶ ህውአትን ለማስወገድ በምናደርገው መራራ ትግል ግንቦት 7ን እንዲቀላቀል አለያም ከጎናችን እንዲቆም ወገናዊ ጥሪውን በድጋሚ ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

---

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት የሶማሊ ልዩ ሚሊሺያዎች በነዋሪዎች ላይ የፈጸሙትን አሰቃቂ ግድያ ይፋ አደረገ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በትናትናው እለት የስርጨት ፕሮግራሙ የሶማሊ ልዩ ሚሊሺያዎች በነዋሪዎች ላይ የፈጸሙትን አሰቃቂ ግድያ ይፋ አድርጓል። ኢሳት ይፋ ባደረገው በዚሁ በምስል የታገዘ ዘገባ እንደተገለጸው በምእራባዊያን አቆጣጠር ማርች 16፣ 2012 በኢትዮጵያዋ የሶማሊ ክልል ፣ በጋሻሞ ወረዳ በክልሉ መንግስት የሚተዳዳሩት ልዩ ሚሊሺያዎች አንድ ወጣት ይገድላሉ። የወጣቱን መሞት ተከትሎ ከወረዳው ህዝብ የተውጣጡ ሰዎች " አሁንስ በቃ " በማለት ገዳዩን የሚሊሺያ አባል ተከታትለው ይገድሉታል። ይህን ተከትሎ የልዩ ሚሊሺያ ሀይሉ አባላት በተደጋጋሚ ወደ አካባቢው በመሄድ ነዋሪዎችን ሲገድሉ፣ ሴቶችን ሲደፍሩና ንብረት ሲዘርፉ መቆየታቸውን የአካባቢው ሰዎች ለኢሳት ማጋለጣቸውን ዘገባው አውስቷል። እንደ ኢሳት ዘገባ "ህዝቡ በቃን" ብሎ እንዲነሳ ያደረገው ዋና ምክንያትም የግፉ ጽዋ ሞልቶ በመፍሰሱ መሆኑን ነዋሪዎች እንደሚናገሩ ታውቋል።

በማግስቱ ማርች 17፣ ከ2 ሺ በላይ የሚሆኑ ልዩ የሚሊሺያ አባላት ወደ ወረዳው ተመልሰው በመሄድ ሰዎችን ከቤት እያወጡ ሰዎችን ገደሉ። ኢሳት የአይን እማኞችን ዋቢ በማድረግ እንደገለጸውና የአካባቢው ነዋሪዎች በፎቶግራፍ አስደግፈው በላኩት መረጃ ከቤታቸው እየተለቀሙ የተገደሉት ሰዎች ብዛት 23 ነው። የልዩ ሀይሉ ድርጊት ያስቆጣው የወረዳው ነዋሪ መሳሪያ አንስቶ ከልዩ ሀይሉ ጋር መታኮስ በመጀመሩ፣ 17 የልዩ ሀይል የሚሊሺያ አባላት ተገድለዋል። የህዝቡ ቁጣ ያስፈራቸው የልዩ ፖሊስ አባላት አካባቢውን ለቀው ወጥተዋል ብሏል። ይሁን እንጅ ውጥረቱ አሁንም ድረስ እንዳለ የአካባቢው ነዋሪዎች ይገልጻሉ ብሏል ኢሳት።

የኢትዮጵያ ሶማሊ የጦርነት ቀጣና ተብሎ በመከለሉ አንድም ጋዜጠኛ ወይም የሰብአዊ መብት ድርጅት ወደ አካባቢው በመሄድ በክልሉ ያለውን ችግር ለማጣራት አልቻለም ያለው ኢሳት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በአካባቢው ገለልተኛ አለማቀፍ አጣሪ ቡድን እንዲላክ ቢወስንም፣ ውሳኔውን በወያኔው አገዛዝ እምቢተኝነት የተነሳ እስካሁን ተግባራዊ ለማድረግ አልተቻለም ብሏል።

ቀጣፊው መለስ ዜናዊ ከ7 አመታት በፊት በሶማሊ ክልል የሚካሄደው ጦርነት በሁለት ሳምንታት ውስጥ ይጠናቀቃል በማለት ለፓርላማ ተናግሮ እንደነበር ይታወሳል።

በሌላ ዜና ከዋልድባ ተሰደው በጎንደር መድሀኒዓለም ቤ/ክ የተጠለሉ 48 ባህታዊያን ታፍሰው መወሰዳቸውን ኢሳት በትናንትናው እለት ገልጿል። የኢሳት የጎንደር ዘጋቢ በስፍራው ተገኝቶ እንደዘገበው ባህታዊያኑ ከጥር 2 ቀን 2005 ዓም ጀምሮ መድሀኒአለም ቤ/ክርስቲያን ውስጥ በሚገኝ አንድ አዳራሽ ውስጥ ከሰዎች ጋር እንዳይገናኙ ተደርጎ በጥብቅ ቁጥጥር ሲጠበቁ መቆየታቸው ታውቋል።

በትናንትናው እለት ባህታዊያኑ ከቀኑ ስምንት ሰአት ላይ በአውቶቡስ ተጭነው ወደ አልታወቀ ስፍራ ተወስደዋል ያለው ኢሳት የአካባቢው ወጣቶች ከባህታዊያኑ ጋር አብረን እንሄዳለን የሚል ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከትሎ አካባቢው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሎ እንደነበር ታውቋል።

መነኮሳቱ ገዳሙን ለቀው የተሰደዱት የጸለምት አስተዳዳሪ የትግራይ ተወላጅ እስካልሆናችሁና የክልሉን መታወቂያ እስካላወጣችሁ ድረስ በገዳሙ አትኖሩም በሚል ስላባረራቸው መሆኑን 31 ባህታዊያን በጋራ ጽፈው ያወጡት መግለጫ እንደሚያሳይ የኢሳት ዘጋቢ መግለጹንና የዚህንም ዘገባ ሙሉ ዝርዝር በዛሬው እለት እንደሚያቀርብ ኢሳት ገልጿል።

# የህወሃት መሪዎች "የኢትዮጵያ ታሪክ እንደገና መፃፍ አለበት!" ይላሉ:: ለምን??

(ከገብረመድህን አርአያ ክፍል 1)

ህወሃት ከጥንሥሱ ጀምሮ እንደተልዕኮ እና መመሪያው ለዘመናት ከብዙ የውጭ ወረራዎች እና ያልተሳኩ የቅኝ ግዛት ጥረቶች በአባቶቻችን ጽኑ ተጋድሎ የቆየውን ኢትዮጵያዊነት ለማፍረስ ፤ ህዝብን በአለም ታይቶ በማይታወቅ የቋንቋ እና የዘር ልዩነት ከፋፍሎ ለብቻው የትግራይን ሪፖብሊክ ለማቋቋም፤ ኤርትራን መገንጠል ፤ ትግራይን ከአማራ ቅኝ ገዢዎች ነጻ ማውጣት፤ ኢትዮጵያ የምትባል በአጼ ምኒሊክ የተፈጠረችን አገር ከአለም ካርታ ላይ ማጥፋት፤ የሚሉ እና ሌሎች ዝርዝር ግቦችን እና አላማዎችን አንግቦ የተነሳ ድርጅት እንደነበር ባለፉት በርካታ አመታት እኔ በግሌ ስገልጽ እና ሳስረዳ ህወሃትም አንዳንድ ጊዜ በግልጽ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በግብር ይህንን እኩይ ምግባሩን ሲያሳየን ቆይቷል:: ይኸው ኢትዮጵያዊነትን ከፊት በመሆን ከውጪ ወራሪዎች በጽናት ተጋድሎ አቆይቷል ብሎ የሚወነጅለውን የአማራ ብሄርን የተመቸው ሲመስለው ከ1971 አንስቶ በቀጥታ በሰሜንጎንደር በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በጸለምት እንዲሁም በሚቆጣጠራቸው የትግራይ ቦታዎች እንዳደረገው በዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ፤ ሳይመቸው ሲቀር ደግሞ በተላላኪዎቹ አማካይነት በጉራ ፈርዳ እንዳደረገው ከአካባቢው አማራን የማጽዳት ስራ ሲያደርግ ይኸው ብዙ አመታት ተቆጠሩ::

ወያኔ ህወሃት የደርግ ስርዓት መዳከምን ጨምሮ ከሌሎች ጉዳዮች መገጣጠም ጋር ተያይዞ በተፈጠረለት እጅግ አሳዛኝ ታሪካዊ ኹነቶች ታግዞ በ1983 ዓ.ም. አዲስ አበባን ሊቆጣጠር ቻለ:: በደደቢት ተቀፍቅፎ በሽምቅ ጥቃት የሚቆጣጠረውን ግዛት በተለያየ ጊዜ እያሰፋ የመጣው ህወሃት በገባባቸው እና አንድ፣ አንድ ጊዜም ተቆጣጥሮ በሚቆይባቸው ቦታዎች በዋናነት ከሚሰራቸው ስራዎች አንዱ የመንግስትን ካዝና ማራገፍ እና መዝረፍ ነበር:: የዚህ ዘረፋ ዋና አስተባባሪ እና ተቆጣጣሪም ስብሓት ነጋ ነበር:: ከስብሓት ጋርም ዘረፋውን ያቀናጁ የነበሩት አርከበ እቁባይ፣ አባይ ፀሃየ እና ሟቹ ክንፈ ገብረመድህን የነበሩ ሲሆን ፤ ዘረፋውን ከላይ ሆኖ በስብሓት በኩል ያዝ እና ይቆጣጠር የነበረው ደግሞ መለስ ዜናዊ እንደነበር በበረሃ በነበርኩበት ወቅት በተለያዩ አጋጣሚዎች የማየት እና በቅርበት የመታዘብ የታሪክ አጋጣሚ ነበረኝ:: ህወሃት በወርሃ ግንቦት 1983 ዓ.ም. አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ ወታደራዊ ቁጥጥር እና የማረጋጋት ስራን ከመስራት ጎን ለጎን በገንዘብ ሚኒስቴር ጠቅላይ ግምጃ ቤት፣ በንግድ ባንክ እና በብሄራዊ ባንክ የነበረውን ገንዘብበጠቅላላው በማጋዝ በሚኒሊክ ቤተመንግስት አስቀመጠ:: እንደወርቅ ያሉ በአይነት የተቀመጡ እና በገንዘብ ሊተመን የማይችል እጅግ ብዙ ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ ቅርሳ ቅርሶችንም ሰብስቦ በዚሁ በቤተመንግስት በጊዜያዊነት ባሰናዳው የዘረፋ ጣቢያ ላይ አከማቸ:: ከማዕከላዊው ባንክ ግምጃ ቤት ተጭኖ ወደዚሁ የዘረፋ ማከማቻ የተወሰደው ወደ 800 ኪ.ግ. የሚመዝን ወርቅ የዘረፋውን ትልቅነት እንደማሳያ ሊጠቀስ የሚችል ነው:: በግንቦት መጨረሻ ሳምንት አዲስ አበባን ተቆጣጥረው ለቀጣይ ሁለት ወራት የተደራጀ እና ከፍተኛ የዘረፋ ስራ ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ በቤተመንግስት ያስቀመጡትን እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብን ጨምሮ በአይነት የተደለደሉ እጅግ ብዙ ብር የሚያውጡ ብርቅ መአድናት እና ቅርሳቅርሶችን በአውሮፕላን እና በመኪና በመጫን ወደ ትግራይ አጓጓዙ:: እንግዲህ ለድርቅ የተመደበ እርጥባንን ከደሃ ጉሮሮ በማህበረ ረድኤት ትግራይ -- ማረት በኩል በመንጠቅ እና በተከታታይም የህወሃት ጦር በገባበት ከተማ እንደዚህ በተደራጀ የዘረፋ ስራ የአገር እና የመንግስትን ግምጃ ቤት በማራቆት በተገኘ ገንዘብ ነው በ እንግሊዘኛው ምጽአረ ቃል ኢፈርት (EFFORT) በትግሪኛ ደግሞ ት.እ.ም.ት. ወይም ትካል እግሪ ምትኻል ትግራይን ለቀጣይ የተደራጀዘረፋ እና የኢኮኖሚ የበላይነት ያቋቋሙት::

ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ የተቋቋሙት መሰቦ ሲሚንቶ፣ አልመዳ ጨረቃጨርቅ፣ መስፍን ኢንጂነሪንግ፣ ሱር ኮንስትራክሽን፣ አዲስ መድሃኒት ፋብሪካ፣ ኢዛና ማይኒንግ፣ ትራንስ ኢትዮጵያ ፣ አፍሪካ ኢንሹራንስ፣ ወጋገን ባንክ ጨምሮ እስከ ቱሪስት አስጎብኚ እና መጽሃፍ ቸርቻሮ የደረሰ የንግድ እና የዘረፋ መዋቅር የተዘረጋው በጠራራ ጸሃይ በተደረገ ዘረፋ እና ኋላ ላይ ያለ ማስያዣ ከሃገሪቱ የመንግስት ባንኮች በብድር ስም በሚወጣ ገንዘብ እንደመሆኑ እነኚህ ኩባንያዎች የሁሉም ኢትዮጵያውያን ንብረቶች መሆናቸው በፍጹም ሊዘነጋ የማይገባው ሃቅ ነው:: ለነገሩ እነ ስብሓት ነጋ በተለይ በረሃ በነበሩበት ወቅት የተለያዩ ከተማዎችን ወርረው ሲቆጣጠሩ ይዘርፉ እና ያዘርፉ የነበረው የመንግስትን ንብረት ብቻም አልነበረም:: መጠኑ ይነስ እንጂ ድርጅቱ መሰሪ የሆነ አላማዬን አይደግፉም ፣ ኢትዮጵያዊ አገር ወዳድነት አላቸው፣ በኤርትራ ጥያቄ ላይ ከህወሃት ሃሳብ ጋር አይስማሙም ብለው የመደቧቸውን ንጹሃን ዜጎችን የተለያየ ስም በመስጠት እና በመወንጀል በሃለዋ ወያኔ(ስውር እስር ቤቶች) በመወርወር ንብረታቸውን ይወርሱ ነበር:: እነኚህ ዜጎች መጨረሻቸው በተለያዩ ጊዜያት ከነኚህ እስር ቤቶች ውስጥ በመውጣት መረሸን ነበር:: ስብሓት ነጋ በተለያዩ አጋጣሚዎች ኢፈርት በኢትዮጵያ ሃብታሙ ድርጅት እንደሆነ እና ህወሃትም ያለ ምንም ማፈር 'ኢፈርት መር ኢኮኖሚ' እየገነባ እንደሆነ ነግሮናል:: በተለያየ ጊዜ በዘረፋ የሰበሰቡት እና ያከማቹት ሃብት መጠን ምን ያህል እንደሆነ አስበውት ይሁን አዳልጧቸው ከሚነግሩን ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ ሊል ይገባል::

እነሆ ላለፉት 22 አመታት ማዕከላዊ መንግስቱን ተቆጣጥሮ ያለው ይህ የአጥፊ ወሮበሎች ቡድን በኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ ሲፈጠር ጀምሮ አጠንጥኖ የመጣውን የጥፋት ተልዕኮ ለማስፈጸም ሲሰራ ሲመቸው በይፋ በህዝብ መገናኛ ብዙሃን ትዕቢት በተቀላቀለው ድንፋታ ሳይመቸው ሲቀር ደግሞ በተጠማዘዘ እና ግራ በገባው የፖለቲካ ፍልስፍና በማደንዘዝ እና ግራ በማጋባት ሲሰራ ኖሯል:: ዛሬ፣ ዛሬ ደግሞ በበረሃ ጀምሮ በተጋነነ፣ ተጠምዝዞ በተተረጎመ እና አንድ፣ አንድ ጊዜም ከሜዳ ተጠፍጥፎ በተሰራ የሃሰት እና ክህደት ሽፍጥ ሲያጠቁት እና ሲያንኳስሱ የኖሩትን የኢትዮጵያ ታሪክ እንደ አዲስ እንጽፋለን ብለው በስብሓት ነጋ በኩል በይፋ ማወጅ ጀምረዋል:: የህወሃት መሪዎች አሁን በስልጣን ላይ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ በ1993ቱ ክፍፍል ከስልጣን የተባረሩትም ጭምር በተለያዩ ጊዜያት ይህን በኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ ያደባ የታሪክ ክለሳ እና እንደ አዲስ የመጻፍ ጉዳይ ላይ በተደጋጋሚ ሃሳባቸውን መስጠት ብቻ ሳይሆን ዋና አቀንቃኝም ሆነው ሰብከዋል:: እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ ያቺ አገር እና በወቅቱ የነበሩ መንግስታት ብዙ አፍሪካዊያን በጭለማ በሚኖሩበት ዘመን እንደ ዜጋ በሰጧቸው በጎ እድል ተምረው ሰው መሆን የቻሉ የትግራይ ምሁራን ፍጹም ምሁራዊ እና የዜግነት ሃላፊነታቸውን በወያኔያዊ ዘረኝነት እና ሆዳቸው ለውጠው የዚሁ እኩይ ምግባር አይዞህ ባይ፣ ምሁራዊ ድጋፍ ሰጪ እና አንዳንድ ጊዜም ፊታውራሪ ሆነው መገኛታቸው ነው:: ከሃገር ውጪ ሆነው አንዳንዶቹም ሃገር ቤት ገብተው ለዚህ እኩይ አላማ ከተሰለፉ ምሁር ተብዬ ዜጎች ውስጥ ዶ/ር ገብሩ ታረቀ፣ ዶ/ር ሰለሞን እንቋይ፣ ዶ/ር አሳየኸኝ ደስታ፣ ጎርፉ ገብረመድህን፣ ዶ/ር ቴዎድሮስ ኪሮስ፣ ዶ/ር ክንደያ ገ/ሂወት ናቸው:: ዛሬ፣ ዛሬ ካሸነፈ ጋር ያደሩ መስሎዋቸው ህሊናቸውን ሸጠው በክህደት ቢኖሩም ነገሮች ዞር ያሉ ለት ለትውልድም ሆነ ለህሊናቸው ምን መልስ ሊሰጡ እንደሚችሉ ያሰቡበትም አይመስልም::

የኢትዮጵያ ታሪክ ፍጹም ጥልቀት ያለው እና በአመዛኙ እምብዛም መከራከሪያ ሳይቀርብበት በግልጽ ባሉና በጽሁፍ ተመዝግበው በተቀመጡ ድራሳናት፣ ቅርሳ ቅርሶች፣ እና መዛግብት አስረጂነት ሊጠና የሚችል እና እስካሁንም በተለይ በውጪ የታሪክ አጥኚዎች በመጽሀፉ መልክ በብዛት የተጻፈበት ነው:: ይህንን ታሪክ አጣም ለመተርጎም እና እነ ስብሓት ነጋ እንደሚሉት እንደ አዲስ ለመጻፍ መነሳት መሞከር ሊሳካ የማይችል ነገር ግን ብዙ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል የመጨረሻው የጥቃት ሙከራ ነው::

በታሪክ ኹነቶች ላይ በታሪክ ምሁራን በኩል ደረጃውን የጠበቀ እናጥብቅ የሆኑ ሳይንሳዊ መንገዶችን በመከተል የትርጓሜ ክርክር ማንሳት ይቻላል:: የተከሰቱ የታሪክ እውነታዎችን በመካድ ታሪክን እንደፖለቲካ ማጥቂያ መሳሪያነት ለመጠቀም መሞከር ግን እጅግ ከፍተኛ መዘዝ አለው:: መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ መቶ አመት ነው ብሎ በይፋ በተናገረ ጥቂት አመታት ውስጥ ኢትዮጵያውያን በይፋ በምርጫ ካርዳቸው የሱን ዘረኛነት አንፈልግም ወግድ ባሉት የምርጫ 97 ማግስት አይኑን በጨው አጥቦ ኑና ሚሊኒየም እናክብር ያለው ክስተት መቼም የሚረሳ አይደለም:: የኢትዮጵያ ታሪክ የሶስት ሺህ አመት ታሪክ ነው ሲባል ዝም ብሎ በአፈታሪክ ወይም በዘልማድ የሚነገር ነገር ሆኖ አይደለም:: የግዛት ስፋቱ ይጥበብም ይስፋ የአገራችን ታሪክ 3000 አመት ለመሆኑ የሚያሳዩ የተለያዩ ማስረጃዎች በመኖራቸው ነው:: ይህንን ሃቅ ለመካድ መነሳት እንደነ መለስ እና ስብሓት እኩይ አላማ አርግዞ የመጣ ቡድን ወይንም ጭልጥ ብሎ አእምሮውን የሳተ ሰው መሆን አለበት:: በውጭ አገራት በፖርቱጋል፣ ግብጽ፣ እስራኤል፣ ጣልያን፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን፣ እና ስፔይንን ጨምሮ በብዙ አገራት የአገራችንን የተለያዩ ዘመናት ታሪክ ሊያሳዩ እና ሊይስረዱ የሚችሉ የታሪክ መዛግብት እና ማስረጃዎች ይገኛሉ::

ዛሬ፣ ዛሬ የኢትዮጵያ ማዕከሉን በዘር እና በሃይማኖት ከፋፍሎ ከመታ እና ካዳከመ በኋላ በዝርዝር ሌሎችን የህብረተሰብ ክፍሎች ወደማጥቃት በስፋት ተሰማርቷል:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ፓትርያርክ አንስቶ ሌላ መሰየም:: የተሰየሙትም በእግዚያብሄር ቁጣ ሲወሰዱ ሌላ ለመሾም ድራማ መስራት፣ ኢትዮጵያዊ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችን የእምነት ትምህርት በካድሬዎች ለመጻፍ መሞከር አማኒያኑም እምቢ ሲሉም መግደል፣ ማሰር እና ማንገላታት የዚሁ ታሪክን የማበላሸት እና እንደ አዲስ የመጻፍ ዘመቻ መገለጫ ኹነቶች ናቸው:: ዛሬ ላይ በዋልድባ ገዳማት ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት ዝም ብሎ በአጋጣሚ የተከሰተ አይደለም ይልቁንስ ቀደም ብሎ ታቅዶበት በሂደት እየተተገበረ ያለው ታሪክን የማጥፋት እና የመደለዝ ዘመቻው አካል እንጂ::

(ክፍል 2 ሳይምንት ይቀጥላል)

## የወያኔ አገዛዝ የቀድሞ የኢትዮጵያ ወታደራዊ መኮንኖችን ከተጠቀመባቸዉ በኋላ እንደሚያስራቸዉ ታወቀ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያ በከፍተኛ ወጪ ያሰለጠነቻቸዉንና ከፍተኛ ወታደራዊ ሳይንስ ችሎታ ያላቸዉን የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር አባላት ሲያሰኘዉ እየተጠቀመባቸዉ ሳያሰኘዉ ደግሞ ተቃዋሚዎችን ትረዳላችሁ እያለ እስር ቤት እንደሚወረዉሯቸዉ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ወታደራዊ ምንጮች ከሰሞኑ በላኩልን ዜና ገለጹ። ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ወያኔ የማይበገር ሰራዊት ገነባሁ ብሎ የሚፎክርበትን የመከላከያ ኃይል ለመገንባት በተደረገዉ ጥረት ዉስጥ ቁልፍ ሚና የተጫወቱትን የቀድሞ ጦር ከፍተኛ መኮንኖች በአንድ በኩል ተቃዋሚ ድርጅቶችን ትረዳላችሁ የሚል በሌላ በኩል ደግሞ የቅንጅትን ወታደራዊ ክንፍ እያጠናከራችሁ ነዉ የሚል ሰንካል ምክንያት በመፍጠር ከ10 እስከ 15 አመት የሚደርስ እስር ፈርዶባቸዉ እያሰቃያቸዉ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

የ1997ቱ ምርጫ ካለቀ በኋላ በተደረገዉ ግምገማ ተቃዋሚዎችን ትረዳላችሁ፤ ህገመንግታዊ ስርአቱን በሀይል ለመናድ ሞክራችኋል በሚልና የጦር መሳሪያ ለቅንጅት ወታደራዊ ክንፍ አቀብላችኋል በሚል የሀሰት ክስ ተከስሰዉ ታጠቅ ጦር ሰፈር ተወስደዉ ከታሰሩት ከፍተኛ መኮንኖች ዉስጥ አምስቱ ኮሎኔሎች ሲሆኑ አንዱ ሻምበል ናቸዉ። የወያኔዉ አቃቤ ህግ ወታደራዊ መኮንኖቹ ላይ ምንም አይነት መረጃ ማቅርብ አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን የቅንጅት ወታደራዊ ክንፍ የሚባል ኃይል በሌለበት ቦታ ንጹህ ዜጎችን የቅንጅት ወታደራዊ ክንፍ አባላት ናችሁ ብሎ ማሰር በፍትህ ስርአት መቀለድ ነዉ ሲሉ የመኮንኖቻቹ ቤተሰቦች ተናግረዋል። የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክረሲ ፓርቲ ተዳክሞ ከጠፉና የታሰሩት የፓርቲዉ አባላት ከተፈቱ በኋላ ወታዳራዊ መኮንኖቹም ይፈታሉ የሚል ከፍተኛ ግምት የነበረ ቢሆንም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ማንሰራራት በተለይ እንደ ግንቦት ሰባት አይነት ድርጅቶች መፈጠር ያስደነገጠዉ ወያኔ ተቃዋሚዎችን ትቀላቀለላችሁ በሚል ወታደራዊ መኮንኖቹ እንደታሰሩ እንዲቆዩ አዟል።

ወያኔ በግፍ ካሰራቸዉ የቀድሞ ጦር መኮንኖች ዉስጥ ኮሎኔል ተስፋ ኃይሉ የሚባሉት መኮንን እስር ቤት አንዳሉ በህመም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሲሆን ስማቸዉ ከዚህ በታች የተዘረዘረዉ መኮንኖች ግን አሁንም እንደታሰሩ ነዉ።

| | | |
|---|---|---|
| ኮሎኔል አበበ አስረስ | ኮሎኔል ተስፋዬ ለማ | ኮሎኔል ጌትነት አድማሱ |
| ኮሎኔል ጎሳዬ ቦጋለ | ሻምበል ካሳሁን | |

የግንቦት ሰባት ድምፅ የአዲስ አበባ ዘጋቢዎች አክለዉ በላኩልን ዜና መሠረት ወያኔ በግፍ ያሰራቸዉ ወተደራዊ መኮንኖች በሙሉ የአማራ ብሔር ተወላጆች ናቸዉ።

## የሚልየኒየሙ ግድብ በያዝነዉ ሚለንየም ዉስጥ ተገንብቶ ማለቁ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የህዳሴዉ ግድብ ግንባታ ለህዝብ ይፋ በሆነበት ወቅት አያሌ የኤኮኖሚ ጠበብቶች፤ መሀንዲሶችና የፋይናንስ አዋቂዎች የግድቡን የገንዘብ ምንጭ፤ ግድቡ የሚሰራበትን ቦታና የግድቡን ተቀዳሚ አላማ አስመልከቶ ብዙ ማረሚያዎችን ለአገዛዙ ባለስልጣናት ያቀረቡ ቢሆንም ሁሉንም ነገር አዉቃለሁ ባዩ መለስ ዜናዉ የግድቡን ግንባታ ከራሱ የግል ታሪክ ጋር ለማያያዝ ባለዉ ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ የግድቡ ግንባታ ያለበቂ ዝግጅት እንዲጀመር አድርጓል። ስለሆነም ይህ በአንድ ሰዉ ፍለጎትና ትዕዛዝ የተጀመረዉ ግድብ ወደፊትም ወደኋላም መጓዝ አቅቶት ባለበት በማዝገም ላይ ነዉ።

## መሪ አልባዉ የወያኔ ሚኒስትሮች ምክር ቤት በስንዴ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ለየት ያለ አስተሳሰብ ያለቸዉና የአገሪቱ ችግር የገባቸዉ አንዳንድ የካቢኔዉ አባላት ደግሞ ችግራችን ስንዴ መግዘት ወይም ማምረት ሳይሆን የገዛነዉን ወይም ያመረትነዉን ስንዴ ለተጠቃሚዉ ህዝብ በሚገባ ማከፋፈል አለመቻላችን ነዉ የሚሉም አልታጡም። ለምሳሌ የወያኔ አገዛዝ እራሱ በሰጣቸዉ መግለጫዎች "በ1.5 ሚሊየን ሄክታር መሬት ላይ ይመረታል ተብሎ የሚጠበቀዉ ከ3 ሚሊየን ቶን በላይ ስንዴ ኢትዮጵያን ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት በስንዴ ምርት ቀዳሚ ያደርጋታል፤ ችግሩ ግን ይህ ብዛት ያለዉ ስንዴም ሆነ ከዉጭ አገር ተገዝቶ የሚመጣዉ ስንዴ ዬት እንደሚገባ አይታወቀም።

ከአንድ ከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣን በተገኘዉ መረጃ መሰረት ገበያ ለማረጋጋት በሚል ሰበብ ስንዴ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየተገዛ አየር በአየር ወደ ሌላ አገር እየተዛወረ በመሸጥ ላይ ሲሆን ግዢውን የሚፈቅዱት፣የሚያስፈጽሙት፤ የሚያጓጉዙትና ብሎም ወደ ደቡብ ሱዳንና አረብ አገሮች እያወጡ የሚሸጡት፣ በዘርና በስጋ ዝምድና የተሳሰሩ የህወሀት ሰዎች መሆናቸው በገልጽ ይታወቃል።

መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረባቸዉ ግዜ ማንም ሰዉ ደፍሮ የማያነሳቸዉ ይንንና ይህንን የመሳሰሉ ጉዳዮች ዛሬ የመወያያ አርዕስቶች እየሆኑ በመምጣታቸዉ ስልጣን ከእጃችን ሊወጣ ይችላል በሚል ፍራቻ ብዙ የወያኔ ባለስልጣኖች አገሪቱን ባዶዋን እያስቀሯት መሆኑን ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ፤ በተለይ ከአገሪቱ በከፍተኛ ፍጥነት የሚኮበልለዉ የዉጭ ምንዛሬ ብዛት ያሰጋቸዉ አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ አዳራ ያሉን የገዢዉ ፓርቲ ከፍተኛ ባለስልጣን የህወሀት አባላት ዝርፍያ በዚህ ከቀጠለ በቅርብ ግዜ ዉስጥ የኢትዮጵያ የዉጭ ምንዛ ካዝና ባዶ ይሆናል ብለዋል።

## ለምርጫ ተብየው የተመዘገበው ሕዝብ ቁጥር እጅግ ከተጠበቀው በታች መሆን ወያኔን አደናገጠ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች በሚያዝያ ወር ለሚካሄደው የአካባቢና የአ/አ አስተዳደር ምርጫ ካርድ መውሰድና አለመውሰዳቸውን በቀጥታ እየተጠየቁ መሆኑን እንዲሁም አንዳንድ አባል ያልሆኑ ነዋሪዎች በካድሬዎችና በደህንነት ሰዎች የኢህአዴግ ዕጩ ሆነው በምርጫው እንዲቀርቡ ግፊት እየተደረገባቸው መሆኑን ምንጮች አመለከቱ፡፡

ለአንድ ወር ተካሄዶ ጥር 21 ቀን 2005 ዓ.ም የመራጮች መደበኛ ምዝገባ ቢጠናቀቅም በተለይ በአዲስ አበባ አስተዳደር የተመዘገበው ሕዝብ ቁጥር እጅግ ከተጠበቀው በታች መሆን ገዥውን ፓርቲ ማስደንገጡን እኒሁ ምንጮች አረጋግጠዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የግንባሩ አባላትና ደጋፊዎች በአዲስአበባ አስተዳደር በሚገኙ ቢሮዎች የሚሰሩ ሰራተኞችን ቢሮ ለቢሮ በመሄድ የምርጫ ካርድ መውሰድ አለመውሰዳቸውን በመጠየቅና በማጣራት ላይ ናቸው፡፡

እንደ ኢሳት ምንጮቻችን ገለጻ ከሆነ ካርድ አልወሰድንም የሚሉትን ሰራተኞች ካድሬዎቹ ለምን እንዳልወሰዱ ምክንያታቸውን በመጠየቅ እንዲወስዱ እያግባቡዋቸው ይገኛሉ፡፡ ይህ ድርጊታቸውም በይፋ የመራጮች መደበኛ የምዝገባ ቀነ ገደብ ከተጠናቀቀና ቦርዱ ካቀድኩት በላይ መራጭ ተመዝግቦልኛል ብሎ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ከገለጸ በኋላ መከናወኑ አስገራሚ አድርጎታል፡፡

አንድ የአስተዳደሩ ባልደረባ ስለሁኔታው ሲያስረዳ "አንድ ካድሬ በግልጽ መጥቶ ምርጫ ካርድ መውሰዴንና አለመውሰዴን ጠየቀኝ፡፡ለምን ትጠይቀኛለህ ስለው ምርጫ ላይ መሳተፍ ለስራ ዕድገትም ይጠቅምሃል፡፡አንተ ደግሞ ጥሩ አፈጻጸም ያለህ ሰራተኛ በመሆንህ ካርድ አለመውሰድህ ሌላ ነገር እንዳያመስልብህ ልመክርህ ብዬ ነው" የሚል መልስ እንደሰጠው አስረድቷል ብሏል ኢሳት፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም ከአራት ሚሊዮን በላይ አባላት አሉኝ የሚለው ገዥው ፓርቲ ወያኔ ኢህአዴግ አባል ያልሆኑ ሰዎችን ለምርጫው ኢህአዴግን ወክላችሁ እንድትቀርቡ ታጭታችሃል በሚል በተለያዩ ቀበሌዎች የሚገኙ ግለሰቦችን በግል ስልካቸው ጭምር በመወትወት ላይ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡

ምርጫ ቦርድ ካቀድኩት በላይ መራጮች ተመዝግበውልኛል ሲል በቅርቡ መግለጫ መስጠቱ የሚታወስ ነው ቢሆንም የኢሳት የደቡብ ዘጋቢ እንደገለጠው ዛሬም ድረስ በክልሉ የምርጫ ካርድ የወሰዱና ያልወሰዱ ሰዎች እየተለዩ ካርድ ሲሰጣቸው መዋሉ ታውቋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org